# ክትክታን ለመከታ፣ ለበጣን ለለማጣ፣ እኔ ግን ስናገር በቀጥታ

(KIC) ጩኸቴን ስማኝ

ሰሞኑን አንዲት መለስተኛ ጽሑፍ የ (KIC) መዘዝ በሚል እዕስ ያተረፈውን መዘዝና አሁንም እያስከተለ ያለውን ጠንቅ ለማስታወስና ብሎም መፍትሄውን ለመጠቆም ከአንድነት ትግላችን አንፃርና በግልም የአንድነት ኃይሉ በጠላት ምት ሳይሆን በውስጣችን ባለው ችግር እራሳችንን እየጎዳን መሆኑን እየታወቀ ዝም ማለቱ አጎብዳጅነት መሆኑን በመገንዘብ ነው።

ስለሆነም ያቺን በደፈናው ያወጣኋት ጽሑፍ አሁንም መመለስና መጎብኘት የነገሩን አሳሳቢነት ለአንዴም ለሁሌም አስምሬበት አልፋለሁ። ግለሰብ ስለዘከረበት ጉዳዩ ከመድረክ አይጠፋም ። ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ለመመለስ መነሻ ያደረኩት በቅርቡ (KIC) በድሕረ-ገጹ ላይ ያውጣውን መግለጫ መሰረት በማድረግ ነው።

ጽሑፉ አሁን ከቅንጅት አፈንግጠው የወጡትንና የትጥቅ ትግልም እንጀምራለን የሚሉትንም ይተቻል፣ እዚያ ላይ እኔም በአመለካከቴ ከተሰነዘረው አባባል የተለየ ስላልሆነ አልተችበትም፣ በሌላው ወገን ግን በነሱው መልካም ፈቅድና ተባባሪነት የተመሰረተ የሚመስለውን (AFD) ን በሚመለከት ግን አሁንም ስሙን እንኳ ሳይጠሩ እንዲያው ሾላ በድፍኑ በማድረግ <u>"የአንድነት ጎራ የተገንጣይ ጎራ ሆኖ እንደማያውቅ ሁሉ ዛሬ የቅንጅት መሪ ከተገንጣዮች ጋር እንደሚተባበሩ አድርገው የሚያሰሙት አሉባልታ ሕዝብን ለማሳሳት በመሆኑ ይህን ጉዳይ ተገንዝበ ሕዝቡ እንዳይቀበላቸው እናሳስባለን"</u> ይላል።

በመጀመሪያ መላው አረፈተ ነገር የሚለው እርስ በእርሱ ይጋጫል፣ "የአንድነት ጎራ የተገንጣይ ጎራ ሆኖ እንደማያውቅ ሁሉ..." የሚለውን አረፍተ ነገር በአዎንታዊ እወስደዋለሁ፣ በኛ በአንድነት ጎራ የነበሩ ወደ ተገንጣዮች ሄደዋል፣ ይሄዳሉም ይህ ሀቅ ነው። ነገር ግን ይህን አረፈተ ነገር "የቅንጅት መሪ ከተገንጥዮች ጋር እንደማይተባበሩ አድርገው የሚያሰሙት አሉባልታ ወዘተ..." የሚለው ከመጀመሪያው አረፈተ ነገር ጋር የሀሳብ ተዋረዱ አልገባኝም። የገባው ካለ ያስረዳኝ።

የቅንጅት መሪ ከተገንጣዮች ጋር ተባብረዋል ወይም ሊተባበሩ ሀሳብ አላቸው የሚል ጥርጣሬ የለኝም። ይህን ካስረገጥኩ በኋላ በ (KIC) ወንድሞቼ አባባልና አፈረጃጀት ቀጥዬ ወደ መሰረታዊ ጥያቄ በሚገባ እዘምትበታለሁ።

<u>አሉባልታ</u>፡-አንድ አስተያየት ሲሰነዘር አሉባልታ የሚያሰኘው ጠባይ እነሆ:-

(1) መሰረት ሳይኖረው “በቅሎ ወለደች” ከሆነ
(2) የተባለውን ሳይሆን ያልተባለውን ካወሩ
(3) ትንሿን ነገር ይዞ “ሰማይ ተሰበረ” ብሎ የሚያወራ
(4) ትንሽም ምሥጢር ያውቅና ሁሉንም ምሥጢር እንደሚያውቅ ሁሉ አፉን በእጁ እየጋረደ ለመንገደኛው ሁሉ “ለሰው እንዳትናገር እያለ የሚዘራ፣ አሉባልተኛ፣ ወንፊት፣ አሽሟጣጭ ይባላል።

እኔ ያቀረብኩበት መንፈስም አሁን የምገፋበት መንፈስ ባልታወቀ ርዕስ፣ በሚሥጢር በተያዙ አጀንዳ፣ ገበያ ላይ ባልዋለ ሸቀጥ፣ የምሰራው አጥቼ ለመሳለቅ አልተነሳሁም። ሸሙጥን በደርግ ጊዜ “ሸሙጥ” ጋዜጣን ያዘጋጁ ለነበሩት የጊዜው ፖለቲከኞች እተወዋለሁ።

የ(AFD) ጥያቄ አሉባልታ አይደለም አሁንም ልድገመውና አሉባልታ አይደለም።

(AFD) ከሚሊዮን በላይ ከአገር ውጪ የተሰደደውን ኢትዮጵያዊ የከፋፈለ ሐጉራዊ ጥያቄ ነው

(AFD) የቅንጅት ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆን እስከ አመራር እርከን ድረስ የከፋፈለ ነው።

(AFD) አሁንም በምናየው ሁኔታ በመንግስታት ደረጃ ቅንጅትንና አባሎችን እየጎዳ ነው።

(AFD) (OLF)ና ሌሎቹ አባል ድርጅቶች አሁንም በፈለጉት ቦታና ጊዜ፣ ለፈለጉት ድርጅትና መንግሥት ዋናው የኢትዮጵያ አንድነት አስጠባቂ ፖርቲ አብረዋቸው እንዳሉ በማድረግ ይጠቀሙበታል።

አዋጁን በሚሥጥር ካላደረግነው በስተቀር ኮሶ እየጠጣን “አሁን ሽሮ፣ ማታ ዶሮ” ማለት እራስን ከማታለል በስተቀር አሉባልታ ተብሎ የቀልማድ ጩኸት ሊባል ባልተገባው ነበር።

የ(KIC) አመራሮችም ሆኑ ሌሎች ያልተገነዘቡት አንድ ነገር አለ። ይህን ሀሳብ በምጠቁምበት ወቅት አያሌ ታላላቅ ሰዎች፣ ምሁሮች፣ አገር ወዳዶች አሁንም በኃይሉ ሻውል ከሚመራው እንቅስቃሴ ውጪ ሌላ እንቅስቃሴም ሆነ ድርጅት ለኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና የቆመ የለም ብለው ከሚያምኑት ጋር ሆኜ ነው። እነዚህ ግለሰቦች በየጊዜው ድምፃቸውን በአደባባይ፣ በግልም፣ በሕብረትም አንስተዋል። አሁንም በ(AFD) ላይ ያላቸው አቋም የማይናወጥ ነው። የነዚህን ሁሉ አስተሳሰብ ነው ለመጠቆምና ተስፋ ከመቁረጣችን በፊት የመፍትሄ ያለህ ያልኩት፣ አሉባልታ ለማናፈስ አልነበረም። አገሬ ኢትዮጵያ ትፍረደኝ።

ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች በኢትዮጵያ አንድነት ዙሪያ የተሰባሰብንና ለዚያውም የምንታገል ሁሉ እንቶፈንቶውን ትተን በአስተሳሰብና በአመለካከት፣ በፖሊሲና በመተክላዊ ጥያቄዎች በየጊዜው ልዩነቶች ይነሳሉ፣ ልዩነቶች በሚነሱበት ጊዜ ገንቢ በሆነ መንገድ ለማየት መጣር ግዴታችን ነው። የልዩነቱን አይነት ሊገፋበት ከሚችለው በላይ መግፋት መቃቃርን ይፈጥራል። በተለያዩ ጥያቄዎች የጠበቀ አቋም ብንይዝም፣ የአንድነት መሰረታችን እስከሚናጋ ድረስ ግትር መሆን የለብንም። ለዚህም ነው በ(AFD) ጥያቄ ላይ በበኩሌ ከዚህ በላይ ለወደፊት አልመለስበትም። ቢሆንም ሁለት ጥያቄዎችን አነሳለሁ።

(ሀ) የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ
(ለ) የትግል ስልት ጥያቄ

(1) - የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ መሠረታዊ የሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ነው። (AFD) ከዚህ አንፃር ስለሚታይና፣ በቀጥታም የተያያዘ ስለሆነ የኢትዮጵያን አንድነትና ህልውና የነካና፣ የሚነካ ስለሆነ ሐረጋዊ ይዘት አለው። ስለሆነም በ(AFD) ውስጥ የተካተቱ (OLF) እና መሰሎቹ ቅንጅትን ሳይጨምር፣ የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት በሁለተኛ ደረጃ፣ የመገንጠልና የራሳቸውን ብሄረሰብ ጉዳይ ቀዳማዊ በማድረግ መተክላዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ያለማወላወል ከ30 ዓመት በላይ የሰሩበትና ከምን ጊዜውም በላይ እየገፉበትም ስለሆነ ሐጉራዊ ግዴታ ያለብን ሁሉ ከዚያ አንፃር እናየዋለን። ስለሆነም ይህ ጥያቄ የቅንጅት ወይም የኢሕአፓ ወይም የሕብረት ወዘተ… ጥያቄ አይደለም። ፖለቲካው ውስጥ ያልገባው የዕለት ጉርሱን ለማግኘት ደፋ ቀና የሚለው የደረቀ ተራራ ሲቧጥጥ የምድረ በዳ አሸዋ በላዩ እየነፈሰ እጆቹን ወደእግዚአብሄር አንስቶ "ኤሎሄ፣ ኤሎሄ" የሚለው የዚያ አንድ ሐገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ጩኸት ነው። ስለዚህ ማንም ፓርቲ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ በሚነሳ ጥያቄ የኔ ነው የሚለው የበላይነት ጥያቄ የለውም። ፓርቲዎች (በአንድነት ጎራ ያሉ) ኢትዮጵያዊ ናቸው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፓርቲዎችም ናቸው። ነገር ግን ኢትዮጵያ የምንላት ሐገራችንም ሆነች ሕዝቧ የፖለቲካ ፓርቲ አይደለም። ኢትዮጵያ ቅንጅት አይደለችም፣ ኢትዮጵያ ኢሕአፓ አይደለችም፣ ኢትዮጵያ ሕብረት አይደለችም። እነዚህን ፓርቲዎች ጨምራ በነዚህ ፓርቲዎች ውስጥ ያልታቀፉትንም፣ ፖለቲካ ምንነቱን የማያውቀው ተራ ገበሬውን፣ ሠራተኛውን፣ የጦር ሰራዊቱን፣ ተማሪውን ሁሉን አቅፋ የያዘች ህልውናዋም በዚያው የሚገለጽ አንድነቷም በፖለቲከኞችን በገለልተኞችም አንድነት ታፍራ ተከብራ የምትሄድ ናት።

ስለሆነም ማንኛውም ፓርቲ እነዚህ የመገንጠል አላማ ያላቸውን ድርጅቶች ከመራቅ ይልቅ በመቅረብ በጽሞና ባማስረዳት የተነሱበትን ዓላማ እንዲቀይሩና ፕሮግራማቸውን እንዲያድሱ ማበረታታት ተገቢ ይሆናል። አድካሚነቱን ከአክራሪዎችና ከጠባቦች መገንጠልን እንደ ሐይማኖት ከያዙ ጋር በቀና መንፈስ መነጋገር ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ሆኖም መደረግ አለበት። ከንግግር አልፎ ስምምነት፣ ግንባር፣ ትብብር በሚል ውል ሲፈረምና አቋም ሲወሰድ መዋቅር ሲወቀር፣ የመንግሥት አያያዝ ሲፈረጅ "የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች" ይሆናልና ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም እንዲሉ ክርክሩም ለበጣውም እየተስተዋለ ቢሆን ቁም ነገሩን ለማስተዋል ይረዳል እላለሁ።

ለዚህ ነው (AFD) እንደ ድርጅት ከተፈረመና ከተዋቀረ በኋላ ለመቀራረብ ነው፣ ለማሳመን ነው ወዘተ... የሚለው ክርክር ከመሬት ሳይነሳ የወደቀው። ይህ በፊርማ የፀደቀው ውል <u>በፊርማ፣ በዶኩመንት፣ በአዋጅ ብቻ ነው የሚፈርሰው</u>። የቅንጅት ማኒፌስቶን በመጥቀስ፣ በዋሽንግተን ዲሲ ንግግርና በመሳሰሉትም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ በተደረጉ የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ መድረኮች ላይ በተሰጠ መግለጫ ላይ በተሰነዘሩ አረፈተ ነገሮች የሚታለፍ አለመሆኑን በ(AFD) ውስጥ ያሉት መሪዎች ሆኑ ከዚያ ውጪ ያሉ ኢትዮጵያውያን ያውቁታል። (KIC) ውስጥ ያሉ ወንድሞቻችን የስምምነት ሰነዶች እንዴት እንደሚሻሩ ጠንቅቀው አያውቁም ብንል እራሳችንን መሳደብና መሪዎቻችንን ዝቅ ማድረግ ነው እላለሁ። ነገር ግን እስከ አሁን በሚሉት ንግግርና ጥቅስ ውስጥ የኢትዮጵያ አንድነትን ከማይፈልጉ፣ ከሚፃረሩ ከማለት ያለፈ በአባባል ደረጃ እንኳን (AFD) ሲሉ አልሰማንም። ሰሚ ጆሮ ያለው ሰምቷል፣ አስተውሏል።

የ(KIC) መሪዎችም ሆኑ አቶ ኃይሉ ሻውል ሁል ጊዜ ከሚናገሩት የምንጠቅሰው ቢኖር ግልፅነትና ለትግሉ ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦችን፣ ሂሶችን፣ ነቀፌታዎችን በደስታ እንደሚቀበሉና በብሩህ ህሊና እንደሚያስተናግዱ ነው። ለጊዜው ይህ ሆኖ ባናገኘውም እኛም እነርሱም እንማማርበታለን፣ ትግሉንም እንገፋበታለን ብዬ አምናለሁ።

(2)- የትግሉ ስልት የ (AFD) ጥያቄ ሲነሳ አንዳንድ ወገኖች ከፓርቲያቸው የትግል ስልት ጋር ያያይዙትና ክርክሩ መቅኖ ያጣል።

"ኩታ በየፈርጁ ይለበሳል" እንዲሉ የትግሉ ስልትም በየፈርጁ ከየመጣበት ፓርቲ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ ጋር ይያያዛል።

በሰላም መታገል፣ በትጥቅ መታገል፣ ሁለገብ መታገል፣ በቀጥታ የእየአንዳንዱ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ምርጫና ይህን በታኝ ጸረ አንድነት የሆነን የወያኔ መንግሥትን ገርስሶ እንዴት አርጎ ሕዝባዊና ሐጉራዊ ሥልጣን እንደሚይዝ የሚተልምበት ራዕይ ነው። ይህን ምርጫውን ይዞ እየአንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ይታገላል። በዚህ የፓርቲዎች ምርጫ ማንኛችንም ልንስማማ፣ ላንስማማ እንችላለን። ለኔ ከሆነ "የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" ነውና ሁሉም በመሰላቸው መንገድ መታገላቸው ደስ ይለኛል እንጂ አልነቅፋቸውም። ይህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫና አመለካከት እንዴት ትግሉን ወደመጨረሻው ግብ አደርሰዋለሁ ብሎ የሚጓዝበት ጎዳና ነው። ነገር ግን በዚህ የትግል ምርጭና ዘዴ ጉዟቸው ላይ በተወሰነ ወቅት ሁኔታዎች ተቀይረው ቢያገኙት፣ የትግል ስልታቸውንም እንደሚቀይሩና ሕዝቡንም በዚያ መንገድ ሊመሩት ቢነሱ የምንቃወማቸው ሊሆን አይችልም።

ለዚህም ነው የፓርቲዎች አመለካከትና (AFD) ይዘት ልዩነቱና ሚዛኑ የተለየ የሚሆነው። በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የምናደርገው ክርክርና በሌሎች ጥያቄዎች ላይ የምናደርገው ክርክር በየቦታው፣ በየፈርጁ ለይተን ማስቀመጥ የምንሻው። መጫሚያ የገባች ሙጀሌ በወቅቱ ተነቅሳ ካልወጣች እያደረች እየዋለች ስትሄድ

ስትበስልና ስትፈርጥ በሰንኮፏ ላይ ሌላ ሙጀሌ ሲገባባት እግርም መሄድ አቅቶት በተረከዝ ሸፈፍ ሸፈፍ እያለ መሄድ ይጀምራልና አሁንም ቢሆን የ (AFD) መዘዝ ያልኩት በሰጣችሁት መግለጫ መሰረት የአሜሪካ መንግሥት እንዴት እንደፈረጃችሁና ጥያቄ ያቀረቡትንም እንዴት ያለ መልስ እንደሰጣቸው፣ ሐዘኔንና ቁጣዬን ለመግለጽ ስል የሰነዘርኩበት አንዱ ምክንያቴ ነው። መዘዙ ልናገረው ልጽፈው ከምችለው በላይ ነው። ትርጉም የለውም። ዋናው ቁም ነገር ቅንጅት ማድረግ ያለበትን ለመጠቆም ነው።

መጀመሪያ ይሰጥ የነበረው መልስ (AFD) የተፈረመው መሪዎቻችን እሥር ቤት ባሉበት ወቅት ነውና አይመለከታቸውም ነበር፣ ቀጥሎ እዚህ ቦታ፣ እዚያ ቦታ ተናግረናል ነው።

(ሀ) ጥያቄው አለ አይለቀንም
(ለ) ጥያቄው ከጠላት ወገን የመጣ አይደለም
(ሐ) (AFD)ን በሰነድ አንስቶ ከዛሬ ጀምሮ የዚህ ስምምነት አካል አይደለንም ማለት በወዳጅ መካከል ጥራትን፣ በጠላት ውስጥ ሽንፈትን፣ ሲያመጣ በድርጅቶችና በመንግስታት ደረጃ ግልጽ የሆነ ሕጋዊ ዶክመንት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

(AFD)ን የተፈራረሙ ሦስቱ ግለሰቦች የጊዜው የውጭ አመራር አባሎች ከአራተኛ ታዛቢ ጋር፣ በራሳቸው ያደረጉትም ከሆነ፣ ያደረጉት ተግባር ሁሉ በማደራጀት፣ ገንዘብ በመሰብሰብ፣ መንግስታትን በማግፀን፣ ስብአዊ ድርጅቶችንና ሰላማዊ ሰልፎችን በመምራት ሲያሳትፉና ሲሳተፉ የነበሩ እንደመሆናቸው መጠን (AFD)ንም ሲፈርሙ ከስልጥናቸው ክልልም ውስጥ ይሁን ውጭ ያደረጉት በቅንጅት ሥም ነው። በቅንጅት ሥም ጥሩ ሥራቸውን የቅንጅት ተግባር ነው፣ እሰዬ ብለን ተቀብለን፣ ስህተታቸውን ግን ቅንጅት አያውቀውም፣ የለንበትም፣ አመራሩ እሥር ቤት ነበር ወዘተ... ብንል በመተክልም ደረጃ ተገቢ አይሆንም፣ ለሁሉም ፍትኀዊ አስተያየት ሊኖረን ይገባል።

በሌላው በኩል እሥር ቤት መሪዎች በነበሩበት ወቅት በሁሉም ወይንም በከፊል መሪዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተስማምተውበት ወይንም ቡራኬ ሰጥተውበት ከሆነ በመሰረተ ሀሳቡ ችግር ሊሆን አይችልም። አሁንም በመጀመሪያው አገባብ ይሁን በሁለተኛው ይፈጸም፣ ስህተት መሆኑ እስከታወቀና እስከታመነበት ጊዜ ድረስ፣ ቅንጅት በቀና ተመልክቶ ያደረገውን ስምምነት ስህተት ያዘለ መሆኑን አሳውቆ በይፋ ከድርጅቱ (AFD) መውጣት ለዘላለም ጥያቄውን መዝጋት ድርጅታዊ አሠራርና ትክክለኛ ተግባር ይመስለኛል። ነገር ግን የነ እከሌ ጥፋት ነው ብሎ ጣት መቀሰር ችግር ሊፈጥር ይችላል (unprincipled) ይሆናል። ይህንን ካልኩ በኋላ...

ቅንጅት ፍጹም ነው ስህተት አይሰራም፣ ይህ ጥፋት እኛን አይመለከተንም የሚሉ ካሉ ወይም የማናውቃቸው ሌላ ምክንያቶች በማቅረብ ቅንጅት ንጹህ ሆኖ እንዳይወጣ ደንቃራ የሆኑ ካሉ የምሰጠው ምክር ቢኖር፦

ቢተው ይተው፣
ባይተው ወዳጅ ይምከረው፣
(AFD) በተነሳ ሁልጊዜ አፈርሳታ! ብዬ እደመድማለሁ።

ውህዳንን ለማቀፍ ብዙሀንን መገፍተር ቅንጅትን ያዳከመዋል። ይሁንብን ካላችሁ ደግሞ “መቼስ ማል ጎደኒ” እንዳሉት ቅሬታችንን ይዘን የአንድነት ትግላችንን አብረን እንቀጥላለን ።

ከሰውነት ዳኜ

ድል ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ!